# አገር እንዴት ሰነበተች ቁጥር 30

መስከረም 1 ቀን 2015 ዓም(11-09-2022)

ከሁሉ አስቀድመን ለመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ በተለይም ለአድማጮቻችን እንኳን ለ2015 ዓም አደረሳችሁ እንላለን።በሰላም አደረሳችሁ ለማለት ግን ሰላም በሌለባት አገር ለሚኖረው ሕዝብ ቀርቶ በውጭ አገር እዬኖረ የሃገሩ ሁኔታ እንቅልፍና ሰላም አሳጥቶት ለሚሰቃዬው ብዙሃን የማይዋጥለት ቀልድና ማሾፍ ይሆናል።ያለፈው ዓመት ለጥቂቶች ደስታና ፍስሓ፣ያዩበት፣ በዘረፋና በተረኝነት የተንደላቀቀ ኑሮ ያሳለፉበት ዓመት እንደሆነላቸው አያጠያይቅም።እንደ እውነቱ ከሆነ የኢትዮጵያ ሕዝብ ብዙ አዲስ ዓመቶችን አስተናግዷል፣አንዱ ዓመት በሌላው ሲተካ ተስፋን ሰንቆ ተቀብሏል፤ያ ተስፋው ግን ተስፋን እዬወለደ ከዓመቱ ጋር ተሸጋገረ እንጂ የሚመኘው ነገር ጠብ አላለለትም።ታዲያ ዓመት ቢቀያዬር የቁጥር ለውጥ ከመሆን ያለፈ ትርጉም የለው አልሆነለትም።ጉዳዩ የዓመቱ ሳይሆን የኛው የራሳችን ከዓመቱ ጋር የሚጣጣም የአስተሳሰብና የቀና ልብ ለውጥ ካለማድረጋችን የተነሳ ጨቋኝ አምባገነኖችና ዘራፊዎች የሚፈልቁበትን ምንጭ ባለማድረቃችን ነው ከሚለው ድምዳሜ ላይ ለመድረስ ተገደናል።በዚሁ በተቸነከረው አስተሳሰባችን በተለይም በተሸከምነው የጎሳ አሰላለፋችን ከቀጠልንበት የአሁኑም ሆነ የሚመጡት ዓመቶች እንዲሁ ለውጥ ሳናይባቸው የመከራ ዓመቶች ሆነው ሊያልፉ ይችላሉ።ሆኖም ግን ዛሬም እንደ ልማዳችን አዲሱ ዓመት ካለንበት ድክመት ወጥተን ሰላምና አንድነት የሰፈነበት፣እንዲሆንልን ልባዊ ምኞታችን ነው።ለዚያም የሚጠበቅብንን የዜጋ ድርሻ ለመወጣት ዝግጁና ፈቃደኞች መሆናችንን ለመግለጽ እንወዳለን።መልካም አዲስ ዓመት!

በአለፉት ዓመታት በተለይም ከአራት ዓመት ወዲህ በአገራችን ውስጥ የሰላም አዬር ሳይነፍስ ሕዝብ በማንነቱና በሚከተለው እምነት የተነሳ ጉልበተኞችና ሰብአዊነት የማይሰማቸው አረመኔዎች በሚፈጽሙበት የጭካኔ እርምጃ ለእልቂት፣ ለመፈናቀልና ለስደት የተጋለጠበት ጊዜ መሆኑ አይካድም።ከሁለት ዓመት ወዲህም እስከዛሬዋ እለት ድረስ እነዚሁ አምባገነንና እራስ ወዳዶች ባመጡት የሥልጣን ንትርክ በጦር ሜዳ ወገን ከወገን ጎራ ለይቶ እዬተላለቀ ይገኛል። ይህንን ጦርነት ለአገር አንድነትና ሰላም የሚደረግ ትግል እንደሆነ አድርጎ በማቅረብ ጠግቦ ያላደረውን፣በድህነት የሚማቅቀውን ሕዝብ በማጭበርበር መብቱን ላላከበረለት በተረኝነት ሥልጣኑን ለያዘው ቡድን ጥቅም በጦር ሜዳ እንዲማገድ አድርገውታል።ወያኔዎቹም እንዲሁ ለ27 ዓመት የት እንደነበር ያላስታወሱት ግን በስሙ የሚነግዱትን ደሃ የትግራይ ተወላጅ በጠባብ ጎሰኝነት ገመድ ተብትበው እንዲሞትላቸው በግድም በውድም አሰልፈውት የጥይት እራት እንዲሆን ፈርደውበታል።ይህ የአሁኑ ጦርነት በሁለት ዓመት ውስጥ ለሦስተኛ ጊዜ ሲሆን ባለፉት ሁለት ጦርነቶች ለሁለቱም ጸረ ኢትዮጵያ ለሆኑት ቡድኖች የጦር ሜዳ እንዲሆን የተፈረደበት የጋራ ጠላት የሆነው የአማራው ተወላጅ የሚኖርበት ከባቢ እንዲወድም፣ ሕዝቡ እንዲያልቅ፣ንብረቱ ወድሞ በድህነት አሮንቃ እንዲዘፈቅ ብሎም እስከዘላለሙ አንገቱን ቀና እናዳያደርግ በስውር የተደረገ ስምምነት ለመሆኑ ብዙ ተጨባጭ ማስረጃዎች ታይተዋል። ወያኔ በተደጋጋሚ አንሰራርቶ በአማራው ክልል ገብቶ የፈጸመው ግፍና ወረራ የዚያው ሴራ ውጤት መሆኑ አይካድም።ከዚያም በመቀጠል ለድርድር የመስዋእት በግ ሆኖ የቀረቡት የአማራው ታሪካዊ መኖሪያ የሆኑት የወልቃይትና ጠገዴ ፣የራያና አዘቦ ለም መሬቶች ነበሩ፤አሁንም ድርድር ቢካሄድ እነዚህ ቦታዎች ለሁለቱ አገር አጥፊ ቡድኖች የእርቅ ጥሎሽ ከመሆን አይድኑም።የነ አብይ አህመድ የኦነግ ኦሕዴድ ብልጽግና ቡድን “በሕገመንግሥቱ መሠረት ይፈታል” የሚለውም አባባል ያንን የጋራ ስምምነት ሕጋዊ ሽፋን ለመስጠት የሚደረግ የመጨረሻው መጀመሪያ ነው።ይህንን ደባ ተከትሎ የአማራው ማህበረሰብየተረከበውንና የሚኖርበትን የአያት ቅድመ-አያቶቹን አጽመ-ርስት በቀላሉ

አሳልፎ ይሰጣል ማለት አይደለም።እንኳንስ አሁን ካለፈው በተሻለ ሁኔታ ተደራጅቶ ይቅርና ቀድሞም ቢሆን መብቱን አሳልፎ ላለመስጠት ትግል ሲያደርግ ኖሯል፤ብዙ መስዋእትም ከፍሏል።አሁንም በመክፈል ላይ ነው።

ወጣም ወረደም ግን በተዋጊ ቡድኖች መካከል በሚፈጠር ስምምነትም ሆነ አንዱ በሌላው ቢሸነፍ ለአገራችንና ለሕዝቡ ሰላም ይወርዳል ማለት አይደለም።ሁለቱም ጸረ ሕዝብና ጸረ ኢትዮጵያ ስለሆኑ ከአንድነት ሃይሎችና ከአገር ወዳድ ኢትዮጵያውያኖች ጋር የሚኖረው ግጭት ይቀጥላል። ጦርነት ከአገራችን መሬት ሊወገድ የሚችለው ጸረ ኢትዮጵያ የሆኑት ወያኔና ኦነግ ኦሕዴድ ብልጽግና ከመሰል የጎሰኞች ስብስቦች ጋር ሙሉ ለሙሉ ካሰፈኑት የጎሳ ስርዓትና ካስተሳሰባቸው ጋር ሲወገዱ ብቻ ነው።

ይህንን እውነት በመካድ በሥልጣን ላይ ያለውን ተረኛ ቡድን ለኢትዮጵያ አንድነትና ለዴሞክራሲ ለውጥ የቆመ አድርገው የሚያስተጋቡ ጥቂቶች አይደሉም።የጎሳ ማንነታቸው ያስተሳሰራቸውና ቅጥረኞች ብቻ ሳይሆኑ በትምህርት ከፍተኛ ደረጃ ላይ ደርሰዋል የሚባሉትም ሳይቀሩ ይህንኑ የተሳሳተ አመለካከት በማራገብ ላይ ይገኛሉ።በጣም የሚገርመው እነዚሁ ምሑር ተብዬዎች በአገር ውስጥ ሆነው ከሚደርስባቸው መከራ ለማምለጥ በፍርሃት ተገደው ከሚያሳስቱት በላይ ሃሳቡን የሚያራምዱት በውጭ አገር በሰላም እዬኖሩ የዴሞክራሲን ትርጉም ያወቁና በዛም የመጠቀም ዕድል ያገኙት ጭምር መሆናቸው ማሳዘን ብቻ ሳይሆን በምሁሩ ላይ ሊኖር የሚገባውን እምነትና ተስፋ የሚያሳጡ ሆነዋል።

በወያኔ መራሹ ኢሕአዴግና በኦነግ ኦሕዴድ መራሹ ብልጽግና መካከል ያለውን ልዩነት ወይም አንድነት ለመረዳት የትምህርት ደረጃን አይጠይቅም ነበር።በመሬት ላይ ፈጦ ከሚታዬው፣ከያዙት የጎሳ ፖለቲካ፣ ከሚመሩበት የጥፋት መመሪያ ሕግና ከዘረጉት የክልል አወቃቀር፣በሕዝብ ላይ ከሚያደርሱት በደል፣ ከሚዘርፉት የአገር ሃብት በመነሳት የስርዓቱን ምንነት ለማውቅ በተቻለ ነበር።ግን ማወቁን እናውቃለን ብንናገር እናልቃለን ወይም የምንፈልገውን እናጣለን ከሚል እራስ ወዳድነት በመነሳት አገርና ሕዝባቸውን ከደው ለአገር አጥፊዎች ማደርን፣ጥብቅና መቆምን መርጠዋል።ይህ የዛሬው አቋማቸው ነገ በህይወት ካሉ የሚያፍሩበት አለያም ለልጅ ልጆቻቸው የሃፍረት ካባ የሚያላብስና ለህሊና ቁስል የሚዳርጋቸው ይሆናል።መንግሥት ይመጣል፣ መንግሥት ይሄዳል፤የማይሄደው አገርና በትውልድ ሰንሰለት ተሳስሮ የሚቀጥለው ሕዝብ ነው።ያለፉትንም ሥርዓቶች የሚያደንቁና የሚደግፉ ነበሩ፣ ከስርዓቶቹ ጋር ወድቀዋል ወይም እንደ እስስት ተለውጠው ከመጣው ጋር በለመዱት መንገድ ቀጥለዋል።ለነዚህ አይነቶቹ አድርባዮች ዕድል የሚነፍግ በሕግ የተደገፈ ሕዝባዊ ፍርድ መስጠት የግድ ይላል።ቢያንስ ቢያንስ ግም የነካው እንጨት አድርጎ ከማህበረሰቡ መነጠል አንዱ ተገቢ ቅጣት ነው፤ እንላለን።

ካለፈው ሰኞ ስንነሳ የአብይ አህመድ ካቢኔ የውጭ አገር ባንኮች በኢትዮጵያ ውስጥ ገብተው እንዲንቀሳቀሱ ውሳኔ አስተላልፏል።ይህ ውሳኔ የውጭ ምንዛሬ ለማግኘት ይረዳል የሚል ሽፋን ቢሰጠውም ምዕራባውያን ከሚያስቀምጡት አስገዳጅ ሁኔታዎች አንዱ ነው።ውሳኔው የአገር ውስጥ ባንኮች ከማይችሉት ጋር ተወዳድረው እንዲወገዱ ከማድረጉም በላይ የአገር ገንዘብ ወይም ብር ዋጋ በውጭ ባንኮች ፍላጎት የሚወሰን ይሆናል።ለራሳቸው ብር ከፍተኛ የምንዛሬ ተመን በማስቀመጥ የማስተካከል እርምጃ(Stractural adjustment)በሚሉት ፈሊጥ ብሔራዊ ባንኩን ያሽመደምዱታል። የገባዬውን ዋጋ በቁጥጥራቸው ስር አድርገው ነጻ ገበያ በሚለው ሽፋን ይጫወቱበታል፤የአገር ኢኮኖሚም በነሱ ውሳኔ የሚመራ ይሆናል።ኢትዮጵያ ከውጭ አገር ለምትገዛቸው ምርቶች መግዣ ዶላር ብዙ ብር እንድታወጣ ትገደዳለች። የጥገኝነት ወይም የነጻነት አንዱና ዋናው መንገድ ብሔራዊ ኤኮኖሚውን አለመቆጣጠር ወይም መቆጣጠር ነው።ለመቆጣጠር ያልታደለ አገር ነጻነት አለው ተብሎ አይቆጠርም።የአገርን የገንዘብ መጠንና ዝውውር የሚቆጣጠረው ብሔራዊ ባንኩ መሆን

ሲገባው በውጭ ባንኮች መዳፍ ሥር ከዋለ የአገር ኤኮኖሚ ያበቃለታል። በቀጣይም ባንኮችና ሌሎቹ የአገር ተቋማት በግል ይዞታነት ስም(Privataization) ብዙ ብር ላላቸው የውጭ አገር ባለሃብቶችና ድርጅቶች ተላልፈው ይሸጡና አገራችን ሰጥቶ ለማኝ ትሆናለች። ሌላው ይዞት የሚመጣው ጣጣ ከበርቴ ነጋዴዎችና ዘራፊ ባለሥልጣኖች ገንዘባቸውን በውጭ ባንኮቹ በማስገባት ባንኩ የሚወሰነው የምንዛሬ ተመን፣1 ዶላር በመቶ ብር ሂሳብ ቢሆን ፣ መቶ ሚሊዮን ብር ያስቀመጠ ነጋዴ ወይም ባለሥልጣን በካርዱ በውጭ አገር ካለው ቅርንጫፍ ባንክ 1 ሚሊዮን ዶላር ለማውጣት ይችላል ማለት ነው።በዚያም ገንዘብ ቤትና ሸር ገዝቶ ተዝናንቶ ለመኖር ይችላል ማለት ነው።1 ሚሊዮን ዶላር ያለው ሰው በምዕራባውያንም ሆነ በሌሎቹ አገሮች የመኖሪያ ፈቃድ የማግኘት መብቱ የተጠበቀለት ነው። ምክንያቱም ያገሩን ኤኮኖሚ ገሎየገባበትን አገር ኤኮኖሚ በማዳበሩ ተግባር ላይ ውሏልና ነው።በዚህ መልክ የኢትዮጵያም ሆኑ የሌላ አፍሪካ፣የኤዥያና የአረብ አገር ዘራፊዎች ዕድሉን በመጠቀም ከፍትሕ እርቀው በነጻነት ለመኖር ችለዋል።ይህ ሁሉ ሲታይ የባንኮች መግባት በተራዘመ ጊዜ ለአገራችን የሚያመጣው ጉዳት እንጂ ጥቅም የለውም።

በአሁኑ ጊዜ አንዳንድ አገራት የዓለም የመገባበያ ገንዘብ ከሆነው ከአሜሪካን ዶላር ለመላቀቅ አማራጭ በመፈለግ ላይ ናቸው።የቅርቡ የሕንድ፣የቻይናና ሩስያም በአንድ የጋራ ገንዘብ የመገበያዬት ስምምነት ላይ መድረሳቸው ከፍና ዝቅ እያለ ከሚያምሳቸው ዶላር ለመላቀቅ ያደረጉት ስምምነት ብቻ ሳይሆን የፖለቲካ ተጽእኖንም ለማሶገድ ነው።ዶላር ገንዘብ ብቻ አይደለም የፖለቲካ ምርኩዝም ነው።ይህ የሩስያ መራሹ እርምጃ ሌሎቹን የኤሽያ አገሮች ቀልብ ለመሳብ ችሏል።ምናልባትም ብዙ አገሮች ሳይቀላቀሉ የሚቀሩ አይመስልም።ለዚያም ነው አሜሪካና ተባባሪ ምዕራባውያን ቀጠናውን በቀውስና በጦርነት እንዲናወጥ ጠብ ያለሽ በዳቦ ብለው የውክልና ጦርነት ለመቀስቀስ እላይ እታች የሚሉት።

ለዶላር ሲሉ ዕዳ ውስጥ መነከርና የውጩን ንግድ በዚያው እንዲተሳሰር ማድረጉ ይዞት የሚመጣው ችግር ሊኖር እንደሚችል ተገንዝቦ ጥንቃቄ ማድረጉ አይከፋም።ይበልጥ ትኩረት ማድረግ የአገር ውስጥ ምርቱንና ገበያውን በማሳደግ ሊሆን ይገባል።በአፍሪካ ደረጃም የከባቢ ንግድ ትስስር ቢጠናከር የአፍሪካ የገበያ ገንዘብ ወይም ከረንሲ ቢፈጠር ከምዕራቡ በተለይም ከአሜሪካ ዶላር፣ ከአውሮፓውያኑ ኤሮና ፓውንድ ጥገኝነት ያላቅቃል።ይህ የእውነተኛ አፍሪካውያን መሪዎችን መምጣት ይጠይቃል።

ወደ አገራችን ባንክ ስንመለስ ባለፉት ጥቂት ዓመቶች ብዙ ባንኮች ተፈጥረዋል።ከቅርብ ጊዜ ወዲህም እንደ ስርዓቱና አገራዊ አወቃቀሩ በጎሳ ማንነት የተቋቋሙ ባንኮች እንዳሸን ፈልተዋል።በሥልጣን ላይ ባለው የሚደገፈው የኦሮሙማው ባንክ ሁሉንም እዬተቆጣጠረ በአጭር ጊዜ ውስጥ የብዙ ቢሊዮን ትርፍ ባለቤት ለመሆን ችሏል።ታላላቅ ያገሪቱ መስሪያ ቤቶችና ተቋማት የገንዘብ ዝውውራቸውን በዚሁ ባንክ ስር እንዲያደርጉ በመገደዳቸው ለብዙ ዓመት ያገሪቱ ኩራት ሆኖ የኖረው የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ለመፈረካከስና ከጨዋታ ውጭ ለመሆን የሚያበቃው ዝግጅት በዚሁ መጀመሩ እንዳልቀረ ብዙ አመላካቾች አሉ።ከዓመት በፊት በንግድ ባንኩ የነበሩትን የሥራ አላፊዎች አንስቶ ከአዋሽ ባንክ በመጡ የተረኛው ኦነግ፣ኦሕዴድ አባላት በሆኑት ሃላፊዎች ማጥለቅለቁ ለዚያ መንደርደሪያ ሳይሆን እንዳልቀረ ብዙዎች ይናገራሉ።የማታ ማታ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በፕራይቬታይዜሽን ስም ለሚገቡት የውጭ ባንኮች ወይም እያበጠ ለመጣው የኦሮሚያ ባንክ ሳይሸጥ የሚቀር አይሆንም።የኦሮሚያ ባንክ ከውጭ ባንኮች ጋር አብሮ የመሥራት ውል በመፈራረም ለነገዋ ኦሮሚያ የኤኮኖሚ ጉልበት ለመፍጠር የሚያበቃም ሂደት ሊሆን እንደሚችል መገመትና እንዳይሳካ ማድረግ ከአገር ወዳዶች ይጠበቃል። ጎን ለጎንም የአማራ ባንክ የሚባል ተቋቁሞ በመንቀሳቀስ ላይ ነው።መሬቱም የጎሳ ፣ባንኩም የጎሳ ፣ ትምህርት ቤቱም የጎሳ ታፔላ መለጠፉ ለበጎ ሳይሆን ለመጥፎ ውጤትና ዓላማ እንደሚሆን ጥርጥር

የለውም።በዚህ አይነት ኢትዮጵያዊነት እዬኮሰሰ ጎሰኝነት ከመተፋት ይልቅ እያደገ መጥቶ አገራችንን እንዳያፈራርሳት ያሰጋል።አቅጣጫውም ያንን ያመለክታል።

ባንኮችን ለተትረፈረፈ ቢሊዮን ትርፍ ያበቃቸው በአገራችን ውስጥ እንደሌላው ከበርቴ አገር በሚካሄደው የምርትና አገልግሎት መስኮችን እድገትና እንቅስቃሴ የተከተለ ሳይሆን፣በዘረፋ በመጠመዱ ነው።ያም ለአስቀማጩ ትንሽ ወለድ ከፍለው ለተበዳሪው ብዙ ወለድ ከማስከፈላቸው ጋር የተያያዘ በመሆኑ ነው።አስቀማጭ 6% ብር ወለድ ሲያገኝ፣ ተበዳሪ 18% ብር ለባንኮች ይከፍላል። የባንኮቹ ትርፍ 12% ይሆናል ማለት ነው።ይህ ያልተመጣጠነ ወለድ በብሔራዊ ባንኩ በኩል ገደብ ሊጣልበት በተገባ ነበር።ከዚያም በላይ መሥራት የሚገባቸውን ሥራ በህጉና ሙያው በሚጠይቀው መሠረት አለመሥራታቸውን፣በሙስና መጠመዳቸውና ይባስ ብሎም በጥቁር ገበያ መዘፈቃቸውን በሥራው ያለፈ ባለሙያ አጋልጧል።ባንኮች ለጥቅም አጋሮቻቸው ለሆኑት ከበርቴዎች ካላቸው ንብረት በላይ ብዙ ሚሊዮን ብር በመስጠት በጥቁር ገበያ እንዲያፈሱት ተደርጎ ከሚገኘው ገቢ ውስጥ የድርሻቸውን (ፐርሰንቴጅ) በመውሰድ የውጭ ምንዛሬው በእጃቸው እንዲገባ ማድረጋቸውን አጋልጧል።በዚህ መጠነ ብዙ የገንዘብ አቅርቦትና መሽከርከር የተነሳ የብር የመግዛት አቅሙ ወይም ጉልበቱ(Purchasing power) እያሽቆለቆለ ግሽበት(inflation) እንዲፈጠር ይሆንና በሕዝቡ ኑሮ ላይ ጉዳት ያደርሳል።ሸማቹ ተጠቃሚ ሕዝብ በአንድ ብር የሚገዛውን በ10 ብር ለመግዛት ይገደዳል ማለት ነው። አባቱ ዳኛ ልጁ ቀማኛ በሆነበት አገር በዚህ የወንጀል ተግባር ላይ የተሰማሩት የዬባንኩ ሃላፊዎች ከብሔራዊ ባንኩ ሃላፊዎች ጋር በመተሳሰራቸው በሕግ ሊጠዬቁ ቀርቶ ከእኩይ ምግባራቸው ሊቆጠቡ አልቻሉም።ይባስ ብሎም ሌብነትና ማጭበርበሩ፣ምግባረቢስነቱ የብልህና የጀግንነት ሞያ ተደርጎ አበጀህ ይባሉበታል።ይሾሙ፣ይሸለሙበታል።

በወያኔና ብልጽግና መካከል የሚካሄደውን ጦርነት ለማስቆም ማይክራመር በተባለው ሰው መሪነት የአሜሪካ መልእክተኛ ቡድን አዲስ አበባ መግባቱ ታውቋል።የወያኔ መጠቃት ያሳሰባቸው አሜሪካኖች በጎን መሣሪያና ስንቅ እያቀበሉ በፊትለፊት የሰላም መልእክተኛ ሆነው መምጣታቸው ብዙም የሚያስገርም አይሆንም።ወያኔ ሲያጠቃ ለተቸገሩት እርዳታ ይድረስ፣ያገልግሎት መስመሮች ይከፈቱ በማለት እዬጮሁ በእጅ አዙር ለወያኔ የትጥቅና ስንቅ አቅርቦት እንደሚያደርጉ እንኳንስ የኢትዮጵያ ሕዝብ ቀርቶ ኢትዮጵያ ውስጥ የምትበር አሞራም ታውቀዋለች።አሁን ደግሞ የሰላም አባት ሆነው ቀርበዋል።የአብይን ስስ ልብ ስለሚያውቁት በገንዘብም ሆነ በሥልጣኑ ምክንያት የሚሉትን እንዲቀበል ለማድረግ እንደሚችሉ ሙሉ ለሙሉ እምነት አላቸው።አብይ በሥልጣኑ ካልመጡበት የኢትዮጵያን ንብረት በጨረታ ስም አሳልፎ ለመስጠት እንደወሰነው ሁሉ ከወያኔ ጋር ተስማምቶ ትግራይን አሳልፎ ከመስጠትና ኦሮሚያ የተባለ አገር ከመመሥረትና ኢትዮጵያን ከማፍረስ አይመለስም። አሁን በጦርነት ውስጥ ተሁኖም ቢሆን ግንባር ቀደም ሆኖ በመዋጋት ላይ ያለውን የአማራ ፋኖ ከማሳደድ አልተቆጠበም። ብአዴን በተባለው የኦህዴድ አሽከር በኩል በብዙ ሽህ የሚቆጠሩ የአማራው ልጆች ፋኖ ተብለው በእስር ቤት ይገኛሉ።በወለጋም ጭፍጨፋው አልቆመም።ይህ ሁሉ የነገውን የኦነግ ኦሕዴድን መዳረሻ የሚያሳይ ነው።አሜሪካኖች ሁለገብ ስልት በመጠቀም በተባበሩት መንግሥታት በኩል ሳይቀር ወያኔን ለማዳን ታጥቀው ተነስተዋል።በጉልበትም ቢሆን የሚፈልጉትን ከማድረግ አይመለሱም። ወያኔ ለነሱ በምሥራቅ አፍሪካ የሚላላክ ውሻ ማለት ሲሆን፣ኢትዮጵያን ለማፈራረስ የሚረዳ መዶሻና ግሬደራቸው ነው።ከዚያም አልፎ ያስቸገራቸውን የኢሳያስ አፈወርቂን አገዛዝ ጥሎ በወደቦቹ ብቸኛ ባለቤት የመሆን ፍላጎታቸው የሚረጋገጠው በወያኔ እንደሆነ ያምናሉ።

ኦነግ AoHeዴድም በበኩሉ ለኦሮሚያ መፈጠር መንደርደሪያውን ከአዲስ አበባ ከጀመረ ውሎ አድሯል።አብይ በሾማት ከንቲባ በኩል ከመስከረም 2015 ጀምሮ በአዲስ አበባ ውስጥ በሚገኙ

ትምህርት ቤቶች በሙሉ የኦነግ ባንዲራ እንዲሰቀልና የኦነግ መዝሙር እንዲዘመር ተወስኗል።ይህ በሕዝቡ በኩል ተቀባይነት እንደሌለው ቀደም ሲል በአንዳንድ ት/ቤቶች የተማሪዎችና መምህራን እንዲሁም የወላጆች ተቃውሞ የቀሰቀሰ ሲሆን በቀጣዩ ለዚህ ውሳኔ የሚሰጠው የሕዝብ መልስ ምን እንደሚሆን የምናዬው ይሆናል።በዚሁ በአዲስ አበባ በሚገኙት ት/ቤቶች ለመመደብ ከኦሮሚያ ክልል የመጡት ከ5ሽህ በላይ መምህራን እስከአምስት የትውልዳቸው ሃረግ ድረስ የስም ዝርዝር እንዲሞሉ ቅጽ መታደላቸው ተሰምቷል።ምክንያቱ ከሌላ ጎሳ የተቀላቀለ የትውልድ ሃረግ መኖር አለመኖሩን ለማወቅና ምናልባት ከሌላ ጎሳ ጋር የተዋለደ ቤተሰብ ከሆነ  ሙሉ ለሙሉ የኦሮሞ ጎሳ ነው ተብሎ ስለማይቆጠር በሥራው ላይ እምነት ሊጣልበት እንደማይችል ከዚያም ባለፈ ወደ ፊት በኦሮሞ ባልሆነው የአዲስ አበባ ነዋሪ ላይ ከሚወሰደው እርምጃ ጥቃት ጋር በተያያዘ ለመለዬት መሆኑ ግልጽ ነው። የከተማዋም ዳርቻ ቦታዎች እንደዚሁ ለኦሮሚያ ክልል መተላለፋቸውና አዲስ አበባ እንደ አሞሌ ጨው እዬተላሰች እንድታንስ መደረጉ ለመዋጥ ቀላልና ማለማመጃ እንዲሆን የማድረግ ስልት መሆኑ መታወቅ አለበት።ነገ ሙሉ ለሙሉ አዲስ አበባ የሚለው ስሟ በፊንፊኔ ተለውጦ ነዋሪውም በዶሴ ውስጥ ጊዜውን በሚጠብቀው የኦነግ መርሃ ግብር መሠረት እዬተለቀመ በጎሳ ማንነቱ ወደተመደበለት ቦታ (ክልል) ተጠርዞ እንደሚሄድ ሊያውቀው ይገባል።

በሰሞኑ አገርሽቶበት የሚታዬው ነገር ቢኖር የኢትዮጵያን ሰንደቅ ዓላማ ምስል አረንጓዴ ቢጫና ቀይ ጥለት ያለው መልበስና መለጠፍ የሚያስቀጣ ወንጀል ሆኖ ብዙዎች እዬተንገላቱ መሆኑ  ነው። በአዲስ አበባም ሎተሪ የሚያዞሩት ድሆች አብዛኞቹ ከጎጃም ክፍለሃገር ስለመጡ የፋኖ ሰርጎ ገቦች ተብለው እዬተለቀሙ ነው።

የወያኔና የኦነግ አገር አፍራሽ ቡድኖች ኢትዮጵያን ለማፍረስ አንዱና ዋናው አስቸጋሪ የሆነው ተቋም የኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ነች የሚለው አቋማቸው አሁንም እንደተጠበቀ ነው።ብዙ ምእመናንን ከመግደልና ቤተክርስቲያናትን ከማቃጠል አልፎ የተዋህዶን ምሰሶ የሆነውን የፓትሪያርኩን መንበር ለማፍረስ ያልተደረገ ሙከራ የለም።ግን በፓትሪያርኩ ጽናትና በምእመናኑ ብርታት በየጊዜው የታሰበው ሴራ ሊከሽፍ ችሏል፤ይህ ማለት ግን ችግሩ እስከመጨረሻው ተወግዷል ማለት አይደለም። በሲኖዶሱ ዙሪያ የተመደቡ የጎሰኞቹ ሥርዓት ደጋፊዎች እስካሉ ድረስ ችግሩ መልኩን እዬለዋወጠ መምጣቱ አይቀሬ ነው።

ይህ ተግባር በሙስሊሙም የእምነት መሪዎችና ተከታዮች ላይ የሚፈጸም ተመሳሳይ መከራ ነው። የእምነት አባቶችን ከመዳፈር አልፎ የማሰርና የማሳደድ እርምጃም ተካሂዷል ፤በመካሄድም ላይ ነው። ሁለቱም የእምነት ተቋማት በጸረ ኢትዮጵያ ቡድኖች  እንዲጠፉ ተፈርዶባቸዋል።ከጥፋት ለመዳን ያላቸው ብቸኛ አማራጭ ምዕመናኑ እጅ ለእጅ ተያይዘው የቀደመ ታሪካቸውን አጠናክረው አገራቸውን በማዳን እምነታቸውን በነጻነትና በእኩልነት የመከተል መብታቸውን ማስከበር ብቻ ነው።በሁለቱም የእምነት ተቋማት ውስጥ ሰርገው የገቡትን አፍራሽና  የጥፋት ተላላኪዎች መንጥረው ማውጣትና መቅጣት ለህልውናቸው ዋስትና ይሆናል።አገር ሳይኖር ሃይማኖትን በነጻነት መከተል ስለማይኖር ኢትዮጵያን በጸሎትም በስለትም  መጠበቅ የሁሉም ግዴታ ነው።

በአለፈው ጳጉሜ 1 ቀን 2014 ዓም የአገራችን እጣ ፈንታ ያሳሰባቸው ጥቂት የማይባሉ የብዙሃን ድርጅቶች ተወካዮች አንድ ላይ በመሆን ድምጻቸውን ለማሰማት በአዲስ አበባ ካዛንችስ ውስጥ በሚገኝ ሆቴል  የጠሩት ስብሰባ እንዳይካሄድ መንግሥት በፖሊስ ሃይል እንደከለከላቸው አሳውቀዋል።ይህ መነሳሳት ይበልጥ እያደገ ለሕዝባዊ ተቃውሞና የለውጥ መጀመሪያ ሊሆን ይችላል የሚል ተስፋ ተጥሎበታል።ስብስቡም ይበልጥ ተጠናክሮ ለመቀጠል ተስማምቷል።ለውጥ ፈላጊው ሁሉ ከዚህ

ሕዝባዊ መነሳሳት ጋር አብሮ በመቆም፣የጎደለው ቢኖር እያሟላ ትግሉ ብሔራዊ መልክ እንዲኖረው ማድረግ አለበት እንላለን።

የብልጽግና ተብዬው ቡድን ይቃወሙኛል የሚላቸውን ጋዜጠኞችና የማህበረሰብ አንቂዎች፣የፖለቲካ ድርጅት አባላትና ተቃዋሚዎቹን ማሳደዱን ቀጥሎበታል።ጎበዜ ሲሳይን በምሽት ከመኖሪያ  ቤቱ፣ማእዛ ሞሐመድን ከሸሮ ሜዳ ገበያ መሃል በጠራራ አፋኞች ወስደው በፖሊስ እስር ቤት ውስጥ ወርውረዋቸዋል።ጥፋታቸው እውነቱን ለምን ተናገራችሁ የሚል ብቻ ነው እንጂ ወንጀል ሠርተው አይደለም።የሚያስቀው ነገር ሁለቱንም ደፋር ጸረ ወያኔና ጸረ ኦነግ ጋዜጠኞች የወያኔ ተላላኪዎች በሚል ወንጀል ከሶ ፍርድ ቤት ማቆሙ ነው።ቀደም ሲል ታፍነው የተወሰዱትም በፍርድ ቤት ትዕዛዝ በገንዘብ ዋስትና እንዲወጡ ቢፈረድም አሻፈረኝ ያለው ተረኛው መንግሥት በሚቆጣጠረው የፍትህ ቢሮ የተሰዬመው ዳኛና አቃቤ ሕጉ ችግር እዬፈጠሩ፣ዳኛ የለም ወይም የክስ መዝገቡ አልተሟላም በሚል ምክንያት በቀጠሮ ላይ ቀጠሮ እዬተሰጠ መከራቸውን ከሚያዩት መካከል ተመስገን ደሳለኝ፣ አዛውንቱ ታዲዎስ ታንቱና በህመም የሚሰቃዬው  ስንታዬሁ ቸኮል ከሚጠቀሱት ጥቂቶቹ ናቸው። ጥቂቶቹ ማለታችንም ብዙሃኑም የኢትዮጵያ ሕዝብ እንደነሱ በጠባብ እስር ቤት ውስጥ  ባይሆንም በትልቁ እስር ቤት በክልል ታስሮ የቁም ስቃይ የሚያይ መሆኑን ለማሳዬት ነው።ልዩነቱ በረጅም ገመድ በታሠረች ዶሮና  በአጭር ገመድ በታሰረችው ዶሮ መካከል  ያለ ልዩነት መሆኑ ነው።ሁለቱም እስረኞች ናቸው። የኢትዮጵያ ሕዝብ በሙሉ የሃሳብ እስረኛ ነው፣ጉልበቶኞች እንደፈለጉ የሚያደርጉት የስነልቦና እስረኛ ነው።መብቱን ተገፎ ተረኞች ግባ ውጣ የሚሉት እስረኛ ነው።ከእስር ኑሮ ለመላቀቅ የግዴታ ሰንሰለቱን መበጠስ ይኖርበታል።በልመናና በፍርሃት የመከራው ጊዜ አያጥርም፤ በኑሮ የሚገረፉበት አለንጋ አይወገድም። ለነጻነቱና ለመብቱ መታገል አለበት።አሳሪውን ሥርዓት ማሶገድ አለበት።ሥርዓቱ እስካለ ድረስ እስረኛነቱ፣መጨፍጨፉ፣መንገላታቱ፣መሰደዱ አይቀርለትም።

አብይ አህመድ የሚመራው ቡድን የኢትዮጵያ ሕዝብን ብቻም ሳይሆን የዓለማቀፍ ማህበረሰቡን ለማጭበርበር የሰላም ቀን  ብሎ ፣ጳጉሜ 3ትን ሰይሟል፣የሰላም መንገድ ብሎም አንድ ጎዳና ሰይሟል። የዛሬው ከትናንቱ፣ መከራው ፣ጭንቀትና ስጋቱ  ይበልጥ አደገ  እንጂ አልቀነሰም።በዚህ መዘላበድ ውስጥ ሆኖ አብይ አህመድ ሰላም ማለት ምን እንደሆነ የማወቅ ችሎታ እንደሌለው አረጋግጧል።እሱ እራሱ ጸረ ሰላም መሆኑን የካደው ይመስላል።እሱ ከሚወክለው ኦነግ ኦሕዴድ ብልጽግና መንግሥትና ካሳደገው ወያኔ  የበለጠ ማን ጸረ ሰላም አለ? የአኖሌን ሃውልት ተክሎ ሕዝብን በቂምና በበቀል ውስጥ መዝፈቁን ረስቶት ይሆን? ነዋሪውን ሕዝብ በጎሳ ማንነቱ እንዲጠቃ የዘረጋውን የክልል አወቃቀርና የሚፈቅደውን ሕገ ጥፋት መሸከሙን ዘንግቶት ይሆን?ከቶ በዬትኛው መለኪያ እነዚህ የሰላም ጸር የሆኑ ድርጊቶች እያሉ ሰላም ሰፍኗል ይባላል?እስኪ ሰላም ወዳድነቱን እነዚህንና የጎሳ ፖለቲካውን በማሶገድ ያሳዬን?እስኪ የአኖሌን ሃውልት የተከልነው በፈጠርነው የውሸት ትርክት ነው ይበልና ያፍርስ?።ያን ጊዜ እኛም ስለሰላም እንናገራለን፣እናወሳለን። ሰላም የሚያናጋ ሥርዓት ባለበት ውስጥ ሆነን ግን ለሰላም መስፈን እንታገላለን እንጂ ሰላም ሰፍኗል ብለን አናወራም።ሕዝብና አገራችንን ከድተን ከአድርባዮችና ከጥቅመኞች ተራ አንሰለፍም።

አብይ አህመድ በአሜሪካኖቹ ጥያቄና በምዕራባውያን ግፊት ብቻም ሳይሆን አማራው በመነሳሳቱ ስጋት ስላደረበት ከወያኔ ጋር የተኩስ አቁም ስምምነት ላይ  ለመድረስ እዬተሸኮረመመ መሆኑን የሚያሳዩ ፍንጮች እዬወጡ ነው።አልፎ ተርፎም ለተወሰኑ ቀናት ተኩስ እንዲቆም አዟል የሚል ጭምጭምታ ይሰማል፤አይሆንም አንልም።ወያኔ ከቦታው ከጠፋ አማራውን እረፍት የሚነሳው ስለማይኖር ፊቱን ያዞርብኛል የሚል ስጋት አለበት።የአማራው መጠናከርና ሃይል ሆኖ መውጣት ለሁሉም ጸረ ኢትዮጵያ ለሆኑት ጎሰኞች የመጥፋት፣ለቀሩት ደካሞች ደግሞ ብርታት የሚሰጥ በመሆኑ ሁሉም ይፈሩታል፤

እንዳይጠነክርም ይረባረቡበታል።ግን አማራው ካወቀበትና ቀዳዳውን ሁሉ ከደፈነ አይሳካላቸውም። አይሆንምን ትተሽ ይሆናልን አስቢ የሚለውን ምክር ወስደን ምን መደረግ አለበት የሚል ጥያቄ ማንሳቱና መልስ መስጠቱ አስፈላጊ ነው።

ስለችግሩ ብቻ ማንሳት መፍትሔ ሊሆን እንደማይችል በማመን የተበታተነው ሕዝባዊ ትግል ተጠናክሮ መቀጠል እንዳለበት ሆኖም ግን ዓላማና ግቡን የነደፈና በግልጽ ያስቀመጠ በእቅድ በሚመራ ድርጅት መኖር አለበት እንላለን።በተወሰኑ ግለሰቦች ፍላጎትና ፈቃድ የሚካሄድ ትግል ለብዙ አደጋ የመጋለጥ ዕድሉ ከፍተኛ መሆኑን መዘንጋት እንደሌለበት እያሳሰብን የከተማው ሕዝብ ወይም ወጣት ለትግል እንዲነሳና ጠላቶቹ በሙሃሪያ ታጅበው ሲያጠቁት ለዱብቻው ከማንባትና ከመበሳጨት ይልቅ በተመሳሳይ ቁመና ላይ ተገኝቶ መታገል አስፈላጊና ወቅቱ የሚጠይቀው ነው እንላለን።ፋኖን ተቀላቅሎ ጠንካራ ሕዝባዊ ድርጅታዊ ቁመና እንዲኖረው ማድረግ ከለውጥ ፈላጊው በኩል ይጠበቃል። በፖለቲካ ትግሉም መስከ የጠራና ኢትዮጵያን ለአንድነትና ለነጻነት ብሎም ለእድገት የሚያበቃ መርሃ ግብር ያለው፣ጸረ ጎሰኝነት የሆነ የፖለቲካ መስመር የሚከተል ድርጅት መውጣት አለበት ።አለበለዚያ ዓላማና ባለቤት የሌለው ትግል ይሆናል።

በትግሉ የአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪ ወሳኝ ሚና እንደሚኖረው ባለፉት ዝግጅቶቻችን የገለጽን ቢሆንም አሁንም እንደግመዋለን።ሕዝብ ድምጹን ለማሰማት ከቆረጠ የሚያግደው እንደሌለ ባለፈው ሳምንት በሡራተኛ እጅ ህይወታቸው ያለፈውን ህጻናት ሞት ተከትሎ ለተቃውሞ የወጣው ሕዝብ አመላካች ነው።በዚህ አጋጣሚ ለህጻናቱ ወላጆች ብርታቱን እንመኛለን።ይህ ጭካኔ የሥርዓቱ ውጤት ለመሆኑ አጠያያቂ አይደለም።የሰው ልጅ የአውሬ ጸባይ እንዲለማመድ ያደረገው ሕጻን ከማህጸን ቀዶ የሚያወጣ ጨካኝ በነጻነት እንዲኖር ያደረገ ሥርዓት መስፈኑ ነው። የአዲስ አበባም ሕዝብ እንደ ሁለቱ ሕጻናት በዱቦታው ለሚታረዱት ወገኖቹ ድምጹን ማሰማት ይኖርበታል።በአንድ ኮንደሚኔም ሰፈር የሚኖር ሕዝብ ለሰፈሩ ነዋሪ ድምጽ ከሆነ በአንድ አገር ውስጥ የሚኖር ሕዝብ ለወገኑ የማይቆረቆርበትና የማይጮህበት ምክንያት አይታዬንም።አለበለዚያ ችግሩ ሰፈር ውስጥ መግባት አለበት ማለት ነው። የአዲስ አበባ ሕዝብ በተጫነው የዝምታ ድባብ ውስጥ ከቀጠለበት ነገ ሁሉም በተራ ሊያርደው ለተዘጋጀው የኦነግ ኦሕዴድ ብልጽግና አውሬ ቡድን ፈቃደኛ ሆኗል ማለት ነው። ሳይቃጠል በቅጠል!

በመጨረሻም ለትግራይ ወገኖቻችን የምናስተላልፈው መልእክት ወያኔ ላለፉት 32 ዓመቶች በጫንቃችሁ ላይ ተቀምጦ በስማችሁ ሲመዘብር ፣አያቶቻችሁ በደማቸውና ባጥንታቸው ዋጋ ከፍለው ያስረከቧችሁን ኢትዮጵያ አገራችሁን ለማፍረስ ደፋ ቀና ሲል፣ከተዋለዳችሁትና አብራችሁ ከኖራችሁት ሕዝብ ጋር አለያይቶ ደም ሲያፋስሳችሁ፣በትግሬነታችሁ ብቻ የወንጀሉ ተሳታፊዎች አድርጎ ሲጠቀምባችሁ፣ በመታለልም ሆነ በመተማመን ለመከራ ሲዳርጋችሁ በማወቅም ሆነ ባለማወቅ የወገናችሁን ደም ለማፍሰስ ሆ! ብላችሁ የምትከተሉ ከሆነ በታሪክ ተጠያቂ ትሆናላችሁ።ይህንን በስማችሁ የሚነግድ ቡድን ከጫንቃችሁ ላይ በማውረድ ከቀረው ኢትዮጵያዊ ወገናችሁ ጋር የነበራችሁን ዘመን ተሻጋሪ ዝምድናችሁን አድሱት።የወልቃይትና ጠገዴ፣የራያና አዘቦ መሬት ብቻ ሳይሆን የመላ ኢትዮጵያ መሬት ባለቤትነታችሁን አስመልሱ።እንደ ወትሮው በፈለጋችሁበት ቦታ ሄዳችሁ ሠርቶ ለመኖርና ሃብት ለማፍራት የሚያስችለውን መብታችሁን በኢትዮጵያዊነት ተራ ተሰልፋችሁ አስከብሩ።እምቢ ለወያኔ ! እምቢ መገንጠል! ብላችሁ ቁሙ።መሰል ድሃ ወገናችሁን፣ ህጻንና እርጉዝ ሴቶችን፣አዛውንት ወላጆችንና መነኮሳትን በመግደልና በመድፈር ከህሊና ቁስልና ከታሪክ ሃፍረት በቀር የሚገኝ ደስታ የለም፣የሚያኮራ ጀግንነትም አይደለም።ከምትታወቁበት የክርስትና እምነታችሁም ውጭ፣የሰይጣን ተግባር መሆኑን ተገንዝባችሁ ንስሃ ግቡ።ለደብረጽዮንና ለጻድቃን፣ ለጌታቸውና ለቴድሮስ አድሃኖም እንዲሁም ለሌሎቹ ስልጣንና ንብረት ሲባል የደሃው የትግራይ ሕዝብ

ልጅ ማለቅ የለበትም ብላችሁ ቁሙ፣ወንጀለኞቹን ተቃወሙ፣አጋልጡ፣አውግዙ፣ለፍርድ እንዲቀርቡ አድርጉ።

በውጭ የምትኖሩ የትግራይ ተወላጆች ወገኖቻችን ሆይ!ምንም ቢሆን ፊደል ቆጥራችኋል እንላለን። ሌላው ቢቀር በየምትኖሩበት አገር የምትዝናኑበት ሰላማዊ ኑሮ፣በማንነታችሁ ሳትገፉና ሳትበደሉ እንደሰው የመኖሩ ጸጋ መጥፎና መልካሙን እንድታውቁና እንድታመዛዝኑ ረድቷችኋል ብለን እናምናለን። ለእኛም እንዲሁ! እነዚህን መልካም ጸጋዎች በአገራችሁ በኢትዮጵያ መሬት ላይ እንዲኖራችሁ ለማድረግ በጎሳ ነቀርሳ በክሎ የሚያጋድላችሁን ፣ለስደት የዳረጋችሁን የወያኔ ቡድን ደግፋችሁ በዬፈረንጅ አገሩ አደባባይ "እምበር ከብለልቲ"! እያላችሁ የካራምቡላ ድንጋይ ይመስል እዬተንከባለላችሁ አስፋልት ከምታጸዱ፣ለፈረንጁ መሳቂያና ለጥቁር ሕዝብ ማፈሪያ ከመሆን ወደ ቀልባችሁ ተመልሳችሁ የትልቅ አገር፣የኢትዮጵያ ባለቤት በሚያደርጋችሁ ትግል ላይ ተሰለፉ እንላለን። በዘመነ መሳፍንት ወይም በአጼዎቹ ጊዜ በነበረ ጭንቅላት ከመመራት የ21ኛው ዘመን አይምሮና ንቃት ባለቤት ሁኑ እንላለን።ለጦርነት፣ ለበለጠ ድህነትና፣ለአገረቢስነት ለሚዳርጋችሁ ለምዕራባውያን ዕርዳታ ከመጮህ ይልቅ ከኢትዮጵያዊ ወገናችሁ ጋር ሆናችሁ ወያኔና ብልጽግና የተባሉት ጸረ ኢትዮጵያ ፣ጸረ ሕዝብ ቡድኖችን አስግዶ በሰላምና በአንድነት መኖር የሚቻልበትን የጋራ ውጤት ተግባራዊ እንዲሆን ለመተባበር ፈቃደኛነታችሁን አሳዩ እንላለን።

የቀውስ ባለቤት የክፋት ሁሉ ምሳሌ የሆኑትን ተከትላችሁ ለናንተ ጥቅም በማያስገኝ ወንጀል ውስጥ አትግቡ ፣ወንጀለኞችንም አትደግፉ እንላለን። በጦርነቱ ጭዳ የሚሆኑትን የድሃ ትግራይ አርሶ አደር ልጆችን አስቡ።ሕጻናትን፣እርጉዝ ሴቶችን፣አዛውንትና መነኮሳትን መግደል፣ ማሰቃዬትና መድፈር ጀግንነት አይደለምና በድርጊቱ አትኩሩ።ግፋ በለው አትበሉ። የወያኔና የኦነግ ኦሕዴድ ብልጽግ መስማማት ወይም ተመሳሳይ የጎሳ ድርጅቶች ስብስብ ሥልጣን ላይ መውጣት ዘለቄታዊ ሰላም አያመጣም።እነሱን በማስገድ የዘላቂ ሰላም ባለቤት የሚሆነው ሰፊው ሕዝብ ነው።እናንተና እኛ፣ ሁላችንም ኢትዮጵያውያን ነን።ስለሆነም እንደ ጤነኛ ሰው አስቡ!እናስብ!

የትግራይ ተወላጅ ሆይ!ከኢትዮጵያዊው የበለጠ ሱዳን ወዳጅ አይሆንህም! ግብጽም አታስብልህም። ብቻህን ነጥለው ሲያገኙህ እንደሚጫወቱብህ አስብ!የችግሩ ሁሉ ምንጭ ኢትዮጵያዊ መሆኑ ሳይሆን በኢትዮጵያ ውስጥ የሰፈነው የጨካኞች ስርዓት መኖሩ ነው።ስለሆነም ሥርዓቱን አስግደን፣አገራችን ኢትዮጵያን ከመፈራረስ ታድገን ለሁላችንም የሚስማማና የሚያስብልን ሕዝባዊ ሥርዓት ለመመስረት አንድ ላይ እንቁም!

የጸረ ኢትዮጵያኖች ፣የጎሰኞች ድንኳን ይፍረስ!

ኢትዮጵያና ኢትዮጵያውያን በአንድነትና በሰላም ለዘለዓለም ይኑሩ!!